## የኢሕአፓ ወክንድ የአውሮፓ ክፍል
## መግለጫ

ላለፉት አሥር ወራት በተለያዩ የአውሮፓ አገሮች የምንገኝ የኢሕአፓ ወጣቶች የመደራጀትን አስፈላጊነት በመረዳት በኢሕአፓ ወክንድ ሥር ሆነን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍኖ ያለውን የዘረኛና የአምባገነን አገዛዝ ግብአተመሬቱ እስኪፈፀም ድረስ ለመታገል በመስማማት በአውሮፓ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅትን በይፋ ለመመሥረት የማደራጀትና የማሰባሰብ ሥራ ስንሠራ ቆይተናል፡ በዚህ መሠረት እነሆ. ከነሐሴ 11 እስከ ነሐሴ 13 ቀን 2004 ዓም ወይም አኤአ ከኦገስት 17 እስከ ኦገስት 19 ቀን 2012 ከተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች የተውጣጡ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት አባላትና የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት በተገኙበት በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ ባካሄድነው ጉባኤያችን በአውሮፓ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት መመስረቱን ልናበስርላችሁ እንወዳለን። በተለይ የታሪክ አጋጣሚውን ልዩ የሚያደርገው የዛሬ 40 አመት ኢሕአፓ በተመሰረተባት ጀርመን ሀገር በአውሮፓ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት በዚቹው ሀገር መመስረቱ ሲሆን ኢሕአፓ በፅናት የሚታገልለትን የኢትዮጵያን ትንሳኤ ከዳር ለማድረስ በፅናት ይታገላል። በኢትዮጵያ የሕዝባዊ ትግል ውስጥ ለወድቁት ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የሕሊና ጸሎት በማድረግ በተጀመረው ይህ ግባዔያችን በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ጥልቅ የሆኑ ውይይቶችን በማድረግ ሰፊ ግንዛቤ ለመጨበጥ የቻልንበት ከመሆኑም በላይ ለለፉት አሥር ወራት ለኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ) በአውሮፓ ምሥረታ ያደረግናቸውን የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚገልጽ ጽሑፍ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ካደረግንባቸው በኋላ በሙል ድምጽ ፀድቆ በሰነድነት እንዲያዝ ተወስኗል።

የጉባዔያችንን ምሥረታ አስመልክቶ ከተለያዩ የኢሕአፓ አካላትና ከድርጅቱ አመራር ኮሚቴ የትግል አንድነት መግለጫና ለምሥረታው የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክት በጉባዔው ላይ ተነቧል።

በመቀጠልም የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታን ከዓለም አቀፍ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ማኅበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በዝርዝር ለመዳሰስ ተሞክሯል። ይህም በወያኔ የሰቆቃ አገዛዝ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለከፋ ድሕነት የተጋለጠ መሆኑንና የሰብዓዊ መብት ረገጣውም እንደዚሁ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መምጣቱን በተጨማሪም የፕሬስ ነጻነቱም ሙሉ በሙሉ መጥፋቱን እንዲያም ሲል በእምነት ተቋማት ውስጥ በመግባት እየፈፀመ ያለውን የሸብር ተግባር በመቀጠሉ ለአብነት ያህል በዋልድባ ገዳምና በአወሊያ የተፈጸመውን ታሪካዊ ግድፈት በጥልቀት በማየት እየተደረጉ ላሉት የመብት መከበር ትግሎች ያለንን ሙሉ ድጋፍ እየገለጽን ጥያቄያቸው ተገቢውን መልስ እንዲያገኝም የበኩላችንን ድጋፍ እንገልፃለን። በተጨማሪም ላለፉት አሥር ዓመታት የወያኔ መንግሥት በሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት አስገኝቻለሁ እያለ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም በረሃብ የሚያልቀው የሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ አሁንም ሀገራችን የፋይናንስ ብድር ከበለጸጉ አገራት እንድትጠብቅ የተገደደች በመሆኑና ብድሯን መክፈል በማትችልበት ደረጃ ላይ መድረሷን በሀዘኔታ ተገንዝበናል። በዚህም ምክንያት አገሪቱን በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ውስጥ እንድትወድቅ ዳርጓታል።

የኢሕአፓና የኢሕአወሊ ተሞክሮ ከድርጅቱ በተወከሉ ጓዶች አማካኝነት በተለይም የወጣቱን የትግል ታሪክና ተመክሮ በተመለከተ ትምህርታዊ ገለጻ ከተደረገ በኋላ በተሳታፊዎች የወጣቱን

የትግል ታሪክና የከፈሏቸውን መስዋዕትነት በጥልቀት ለመቃኘት ተሞክሯል የትግል ልምድም ቀስመንበታል። ከዚህ የትግል ተሞክሮ ወክንድ በአውሮፓ መከተል ያለበትን የትግል አቅጣጫ በጥልቀት በመዳሰስ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ወስዶበታል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ ወጣቶች ጉልህ ሚና እንደነበራቸውና ዛሬም ይህንኑ ፈለግ በመከተል የወያኔን አገዛዝ ገርስሶ ለመጣል ትግሉን ለማፋፋም ወስነናል።

ከዚያም በመቀጠል የመደራጀትን ጥያቄ ትኩረት በመስጠት ከኢሕአፓ የትግል ተመክሮ አኳያ ድርጅት ምንድንነው? ድርጅት ለምንስ ያስፈልጋል? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ ተወያይተን ሰፊ ግንዛቤ ወስደንበታል። ያለ ድርጅት ትግል ግቡን ሊመታ እንደማይችልም የኢሕአፓ የትግል ታሪክ የድርጅትን ምንነት በሰፊው አስገንዝቦናል። በመሆኑም እንደ ኢሕአፓወክንድ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ሂደት ውስጥ ድርጅቱ ቁልፍ ሚና እንደሚወስድ ሰፊ ግንዛቤ ወስደናል።

የኢሕአፓወክንድን ውስጠ ደንብ በጥልቀት ከመረመርን በኋላ የኢሕአፓን መሰረታዊ ራዕይና አላማ እንዲሁም ተግባሩ ላይ መሰረቱን በመጣል ጉባኤያችን በሙሉ ስምምነት ሰነዱን አጽድቀነዋል። በዚህ ላይ በመመስረት በአሁኑ ወቅት የመለስ አገዛዝ እየደረሰበት ባለው ሕዝባዊ ተቃውሞ ሥረ መሰረቱ እየተናጋ ባለበት ሁናቴ የኛ በኢሕአፓ ጥላ ስርና አመራር ተደራጅተን ትግሉን ስኬታማ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል። ለዚህ ቀና ሂደት የወጣቱ ድጋፉን ትብብር እንደማይለየንም ፅኑ እምነታችን ነው።

በመጨረሻም ጉባኤያችን የሚቀጥለውን የሥራ ዘመን የሚያስተባብሩልን የአመራር አባላት ከመካከላችን በሙሉ ስምምነት በመምረጥ ጉባዔያችን በተሳካ ሁናቴ ተጠናቋል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
በተባበረ ትግላችን እናቸንፋለን!!

19.08.2012